ከሙስና የጸዱች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 24 ነሀሴ 15/2017 ዓ.ም

## በውስጥ ገጾች

ተቋሙ የሥነምግባር ጥሰት በፈፀሙ 92 አመራርና ሰራተኞች ላይ እርምጃ
ገጽ 2

የይዞታ ካርታ አዘጋጃለሁ በሚል 50 ሺህ ብር ጉቦ የተቀበለ የይዞታ ማረጋገጥና ምዝገባ ባለሙያ በቁጥጥር ስር ዋለ
ገጽ 5

የስብዕና መገንቢያ ማዕከላቱ ወጣቶች ክህሎታቸውንና ምግባራቸዉን እንዲያዳብሩ አስችሏቸዋል
ገጽ 5

## ዜጎች ላይ የመልካም አስተዳደርና የሙስና በደል የሚያደረሱ አመራር እና ሰራተኞችን ለመታገል ቆርጠን ተነስተናል- ብልፅግና ፓርቲ





የብልጽግና ፖርቲ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን ባካሄደበት ወቅት ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንደሚታገል ገልጿል።ፓርቲው ባወጣው መግለጫ "በየተቋማቱ ተመድበው የዲሲፐሊን ጉድለት፣ሙስናና የአስተዳደር በደል የሚያደርሱ የሥራ መሪዎችንና አገልጋዮችን ለመታገል ቆርጠን ተነስተናል "ሲል ገልጿል። ሕዝብን እያማረሩ ያሉ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለመቅረፍ እና የሕዝብን ዕርካታ ለመጨመር በትኩረት እንደሚሰራም አስታውቋል።

## መንግስት በስፋት የሚስተዋለውን አነስተኛ ሙስና ለመንቀል እየሰራ ነው - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር)



መንግስት በስፋት የሚስተዋለውን አነስተኛ ሙስና ለመንቀል እየሰራ ነው - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር)

አዲስ አበባ፣ ነሐሴ 14፣ 2017 (ፌ.ሥ.ፀ.መ.ኮ) ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) "የመደመር መንግስት" የተሰኘውን መፅሐፋቸው በማስመልከት ከፋና ሚዲያ ኮርፖሬሽን ጋር ባደረጉት ቆይታ፣ ዋነኛ ሀገራዊ ፈተና የሆነውን ሌብነት ዘመናዊ አሰራር በመዘርጋት ለመቀነስ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሙስና ሰዎች ስልጣናቸውን በመጠቀም በነጻ መስጠት ያለባቸውን አገልግሎት ለሃብት ማከማቻነት ሲጠቀሙበት መሆኑን ጠቅሰው የመንግስት ሰራተኞች የተሰጣቸውን አደራ ወደ ጎን በመተው ለሚሰጡት አገልግሎት ሲያስከፍሉ መሆኑን ገልጸዋል።

ሰዎች ያላቸውን የትኛውንም ሙያ እንደመሳሪያ በመጠቀም አላስፈላጊ ጥቅም ለማግኘት ሲሞክሩ ይስተዋላል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህም አነስተኛ ሙስና እንደሆነ ተናግረዋል።

የመደመር መንግስት ይህን አይነቱን

ወደ ገጽ 2 ዞሯል...

# ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒ.ኤች.ዲ.) በኢትዮጲያ የኳታር አምባሳደር ከተከበሩ ሳድ ቢን ሙባረክ አል ናሚ ጋር ተወያዩ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒ.ኤች.ዲ.) በኢትዮጲያ የኳታር አምባሳደር ከተከበሩ ሳድ ቢን ሙባረክ አል ናሚ ጋር በአለም አቀፍ እና አገራዊ የፀረ-ሙስና ጉዳዮች ላይ ተወያዩ። በቀጣይም ከኳታር የፀረ-ሙስና ተቋም ጋር በጋራ በሚሰሩባቸው ጉዳዮች ላይ የስምምነት ሰነድ ለመፈራረም ተወያይተዋል።







## ከሙስናና ብልሹ አሰራር ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመቅረፍ በትኩረት ሊሰራ ይገባል፡-

ዶ/ር ብሩክ ታዬ

ከሙስናንና ብልሹ አሰራር ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመቅረፍ በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶ/ር ብሩክ ታዬ ገለፁ።

ዋና ሥራ አስፈፃሚው ይህን የገለፁት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የ2017 በጀት ዓመት አፈፃፀም እና 2018 በጀት ዓመት ዕቅድ የተገመገመ እና ዉይይት የተደረገ ሲሆን በ2017 በጀት ዓመት የነበረው መልካም አፈጻፀም በ2018 በጀት ዓመትም በተሻለ ደረጃ መፈፀም እንደሚገባ ያስታወቁት ዶ/ር ብሩክ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

የተቋሙን 2017 በጀት ዓመት አፈፃፀም እና የ2018 ዕቅድ ከአህጉራዊ እና ዓለማቀፋዊ አዝማያዎች አንፃር የአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ኢንጅነር ጌቱ ገረመው በዝርዝር አቅርበዋል። ባለፈው 2017 በጀት ዓመት የተሻለ መፈፀም እንደተቻለ በሪፖርታቸው ያመላከቱት ኢንጅነር ጌቱ፤ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ላደረገላቸው ድጋፍና ክትትል በተቋሙ ስም አመስግነዋል።



በውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር የኢነርጂ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ እና የተቋሙ የቦርድ አባል ዶ/ር ኢ/ር ሡልጣን ወሊ በበኩላቸው፤ ተቋሙ ከፋይናንስ እና ከውስጥ አሰራር አንፃር አዎንታዊ ለውጥ ማምጣቱን ተናግረዋል።

የዳታ ማይኒንግ ስራ ለተቋሙ ትልቅ የፋይናንስ አቅም የሚፈጥር መሆኑን ተናግረው ሁለቱ ተቋማት ተናበው በመስራት የሚፈለገውን ኃይል ማቅረብ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

በግምገማው በውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር የኢነርጂ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ እና የተቋሙ የቦርድ አባል ዶ/ር ኢ/ር ሡልጣን ወሊ፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመት ሆልዲንግ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶ/ር ብሩክ ታዬ፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ኢንጅር ጌቱ ገረመው እና የሁለቱ ተቋማት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

# ቅንጅታዊ አሰራርን በማሳደግ የኮሚሽኑን ተልዕኮ ማሳካት ይገባል፡-

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን

የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጀነራል ካውንስል ከፌደራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በወረደው የ 2018 ዕቅድ እና በ 2017 በጀት አመት ከባለ ድረሻ አካላት ጋር በቅንጅት የተሰሩ ስራዎች ላይ ውይይት አድርጓል፡፡

የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ጀማል ረዲ ስራዎችን ውጤታማ ሊያደርግ የሚችል እቅድ በማዘጋጀትና ተግባራዊ በማድረግ የፀረ ሙስና ትግሉን ውጤታማ ማድረግ ይገባል ሲሉ በውይይቱ ወቅት ተናግረዋል። ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን ማሳደግ ላይ የነበሩን ጠንካራ ጎኖች ማስቀጠል ይገባል ያሉት ኮሚሽነሩ በቀጣይ በጋራ በሚሰሩ ስራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

ምክትል ኮሚሽነር ዘገየ በላይነህ በበኩላቸው የኮሚሽኑን ዕቅድ ሊያሳካ የሚችል ስልቶችን በመንደፍ ውጤታማ ተግባራትን ማከናወን ይጠበቅብናል ብለዋል። አያይዘውም በበጀት ዓመቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተጀመሩ ሥራዎችን ይበልጥ ማጎልበት ይኖርብናል ብለዋል፡፡ ጀነራል ካውንስሉ በመጨረሻም የ2017 በጀት ዓመት የምዘና ሂደትና በኮሚሽኑ በተጠና የሙስና መከላከል ጥናት ላይ ውይይት በማድረግ የቀጣይ ስራ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡





# የፀረሙስና ትግል ውጤታማነት ለማረጋገጥ የኮሚሽኑ አመራርና ሠራተኛ ቁርጠኝነት የሚጠይቅ ነው-ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒ.ኤች.ዲ)

የኮሚሽኑ አመራር እና ሰራተኞች በ2017 በጀት አመት አፈፃፀም እና በ2018 በጀት አመት እቅድ ላይ ውይይት የተካሄደ ሲሆን የ2017 የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናት መሪ ሥራ አስፈፃሚ በሆኑት በአቶ ገዛኸኝ በጋሻዉ የቀረበ ሲሆን ሲሆን በመድረኩ ላይ የተገኙት የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒ.ኤች.ዲ) እንደገለፁት፣ የፀረ-ሙስና ትግል ውጤታማነት የሁሉንም አካል ቁርጠኝነት የሚጠይቅ መሆኑን ገልፀዋል። ከዚህ አንፃር መንግስት ለትግሉ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ጠቁመው በበጀት ዓመቱ 26 ዘርፍ-ተኮር የሥልጠና ሞጁል በማዘጋጀት እና ከመንግስት ከፍተኛ ት/ት ተቋማት በተለዩ ተባባሪ አሰልጣኞች ምልመላና ስምምነት በማከናወን ለተቋማት ከፍተኛ አመራሮችና ሠራተኞች ሥልጠና መስጠት የተቻለ ሲሆን ፣በፀረ-ሙስና ህዝብ ግንዛቤ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሥነምግባር አምባሳደርነት ውድድር ለማካሄድ ታቅዶ የሥነምግባር ክበባትን የማደራጀት፣ የማወዳደሪያ ፕሮቶኮል የማዘጋጀት፣ የሥነምግባር አምባሳደር መለያ የመመዘኛ መሥፈርት የማዘጋጀት ሥራ በመስራት በ48 ዩኒቨርሲቲዎች የሥነምግባር አምባሳደርነት ዉድድር ማካሄድ እና ዕዉቅና የመስጠት ሥራ ተከናውኗል። በዚህም 220 ወጣት ተማሪዎች በማሳተፍ ለዩኒቨርሲቲዎችና ተማሪዎች የዕዉቅና ሰርቲፊኬት እና ሽልማት የተበረከተ መሆኑንና 220 ተማሪዎች በሥነምግባር ዙሪያ ቤተሰብ እና ተቋም-ተኮር የክረምት በጎ ፈቃድ ሥራዎች እንዲሳተፉ መደረጉን ገልፀዋል፡፡

በተመሳሳይ በሙስና መከላከል ጥናት ዘርፍም በበጀት ዓመቱ በተቋማት ከፍተኛ የሙስና ተጋላጭነት ሥጋት ሆኖ በተለዩ አምስት አገራዊ ጉዳዮች በመለየት የጥናት የተከናወነ ሲሆን በተጠናዉ ጥናት መሠረት ምክረ-ሐሳብ ለተቋማት ከፍተኛ አመራሮች ቀርቦ ወይይት መደረጉን እና በቀጣይ አፈፃፀሙ ክትትል እንደሚደረግበት ተገልፀል፡፡ በተጨማሪም በቁጥር 153 ለሚሆኑ በአዲስ ለተመደቡ የስነምግባር መከታተያ ክፍል ሰራተኞች በስነምግባር እና ሙስና ምንነት፣በሙስና ወንጀል ህግ፣በሀብት ምዝገባ አዋጅ፣በጥቆማ አፕሊኬሽን አተገባበር እና በዘርፍ ፎረም አደረጃጀትና አሰራር ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል።



የ2018 በጀት አመት እቅድ ደግሞ በኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታ ሥልጠና መሪ ሥራ አስፈፃሚ በሆኑት ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር ቀርቦ ዉይይት የተካሄደ ሲሆን በመድረኩ ላይ የተገኙት የሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ፍቃዱ ሰቦቃ የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም በሥነምግባር ግንባታ ስልጠና በህዝብ ግንዛቤና ከተቋማት ሥነምግባር መከታተያ አደረጃጀት አንፃር ጥሩ አፈፃፀም የነበረበት ዓመት መሆኑን በመግለፅ ለ2018 በጀት አመት የታቀዱ የፀረ-ሙስና ትግል ተግባራት በቁርጠኝነት ለመፈፀም ሁሉም በጋራ እና በቅንጅት መረባረብ እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

በሌላ በኩል የኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ዘርፍ ም/ኮሚሽነር እሸቴ አስፋዉ በሙስና መከላከል ጥናት ፣በዲጅታል ሀብት ምዝገባ እና በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራዎች የተሻለ ሥራ የተሰራበት በጀት ዓመት መሆኑን በመግለፅ በቀጣይ በጀት ዓመትም በታቀደዉ ዕቅድ መነሻ በማድረግ ሙስናን መከላከል መሠረት ያደረገ ሥራ ለመስራት ሁሉም በቁርጠኝነት እንዲሰራ አሳስበዋል፡፡

በመድረኩ ማጠቃለያና የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድን አስመልክቶ ማብራሪያ የሰጡት የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) በሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ በተመለከተ ዘርፍ-ተኮር የሥልጠና ሞጁል አዘጋጅቶ በማፀደቅ እንዲሁም የበየነ መረብ ሥልጠና ቪዲዮ በማዘጋጀት በስነ ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ዙሪያ ከ48 ሺ በላይ አመራርና ሰራተኛ ስልጠና እንደሚሰጥ፣ 500 ለሚሆኑ የግል ኮሌጆችን ጨምሮ ከከፍተኛ ት/ት ተቋማት ለተለዩ ተማሪዎች የሥነምግባር አምባሳደር የአቅም ግንባታ ስራ እንደሚከናወን ፣ከ8 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ እንደሚፈጠር እና በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ያሉ ከ10 ሺ በላይ ለሚሆኑ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የትስስር ፎረም በመመስረት የአቅም ግንባታ ስልጠና እንደሚሰጥ እና ከወዲሁ ትኩረት ተደርጎ መሰራት እንዳለበት አቅጣጫ ሰጥተዋል፡፡

በተመሳሳይ ኮሚሽነሩ አክለዉም በሙስና መከላከል ጥናትና ክትትል ዘርፍም ወደ 8 የሚሆኑ የሙስና መከላከል ጥናት እንደሚካሄድ፣በዲጂታል ሀብት ምዝገባ (EARS) በመታገዝ በ26 ዘርፎች የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ መረጃ ትንተና እንደሚከናወን እና በ10 ዘርፎች የሀብት መረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሥራ እንደሚሰራ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ዜጎች ዲጅታል የሙስና ወንጀል መጠቆሚያ NCRS በመጠቀም እንዲጠቁሙ ሰፊ ሥራ እንደሚሰራና የአስቸኳይ የሙስና መከላከል (የማቋረጥ) ሥራዎች ተጠናክረዉ እንደሚቀጥሉ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡





## ከገጽ 1 የዞረ...

ሌብነት በአረም መልኩ እንደሚመለከተው ጠቅሰው፥ አረምን ለይቶ ማወቁ ለመንቀል ቀላል ቢያደርገውም ብዛቱ እና ከማሳው ጋር መመሳሰሉ ስራውን አታካች ያደርገዋል ብለዋል፡፡

ይህ አይነቱ ሌብነት ብዙ እና ለልየታ አዳጋች ቢሆንም ከተለየ ለመንቀል ቀላል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ሌላው የሌብነት ዓይነት ከባድ ዝርፊያ መሆኑን በመጥቀስ በግለሰቦችና ቡድኖች መካከል በቅንጅት የሚሰራ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ይህም አንዳንዶች ስልጣን ይዘው፣ አንዳንዶች ሚዲያ ይዘውና ሌሎች ደግሞ የጦር መሳሪያ ይዘው የሚፈጽሙት የተቀናጀ ዝርፊያ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

መንግስታት ከባዱን ዝርፊያ ቢመለከቱ እንኳን ለመንቀል ያስቸግራቸዋል ነው ያሉት፡፡

መሰል ዝርፊያዎች እንደ ዋርካ የሚታዩ ሆኖም ግን በቀላሉ ለመንቀል የሚያዳግቱ ሲሆን በሀገር ደረጃ ካደጉ የመንግስትን ፖሊሲና አቅጣጫ የሚወስኑ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ይህም በተለያዩ ሀገራት እንደሚታይ አንስተው፥ በኢትዮጵያም ከለውጡ በፊት በግልጽ ሲታይ እንደነበር አስታውሰዋል፡፡

ባለስልጣናት ከባለሃብቶች ጋር ተመሳጥረው ህግ ሲያወጡና ያሻቸውን ሲዘርፉ የነበሩበት ሁኔታ ነበር ነው ያሉት፡፡

ከለውጡ በኋላ በተሰራው ስራ መሰል ዝርፊያ አለመኖሩን ተናግረዋል፡፡

የመደመር መንግስት በስፋት የሚስተዋለውን አነስተኛ ሙስና ለመንቀል ስርዓት ዘርግቶ ለማስወገድ በስፋት እየሰራ ነው ብለዋል፡፡

በመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎትን ጨምሮ ሞባይል ባንኪንግና ዘመናዊ ግብይቶች መፈጠራቸው ችግሩን እንደሚቀርፍም አመላክተዋል፡፡



## ኮሚሽኑ የሙስና ጥቆማዎችን ዘመኑ በደረሰበት ቴክኖሎጂ በመታገዝ እየተቀበለ እንደሚገኝ አስታወቀ

የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የሙስና ጥቆማዎች ዘመኑ በደረሰበት ቴክኖሎጂ በመታገዝ እየተቀበለ እንደሚገኝ አስታወቀ።

ኮሚሽኑ የሙስና ጥቆማዎች ከወረቀት ንክኪ የፀዱ ለማድረግ በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል ሲል ገልጿል።

የጥቆማ ሰጪዎችን ጊዜ፣ ገንዘብና አላስፈላጊ ምልልስን ለመቅረፍ በቴክኖሎጂ የታገዘና ከወረቀት ንክኪ የተላቀቀ ስርዓት መዘርጋቱን የገለፀው ኮሚሽኑ ይህንን አገልግሎት ለሚያስተዳድሩ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠቱን አስታውቋል።

ስልጠናው ከኢትዮ ቴሌኮም በመጡ ባለሙያ የተሰጠ ሲሆን የለሙ ቴክኖሎጂዎችን የሚያስተዳድሩ ባለሙያዎች ክህሎታቸውን ለማሳደግ ያለመ መሆኑ ተገልጿል።

ቴክኖሎጂው በድምፅ፣ መልዕክትና ቀጥታ በመደወል የሚሰራ ሲሆን በተጨማሪም መረጃዎችን በቀላሉ ለመላክና ለመቀበል ከማህበራዊ ትስስር ገፅ ጋር የተሳሰሩ መሆናቸው ለማንኛውም ሰው ተደራሽ እንዲሆኑ ያስችለዋል።

## በ2017 ዓመት ከ418 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት የመንግስት ሐብት ከምዝበራ ማዳን መቻሉን ገለፀ፡- የደቡብ ወሎ ዞን ፍትህ መምሪያ

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከ418 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት የመንግስትን ሀብት ማዳን እንደተቻለ የደቡብ ወሎ ዞን ፍትህ መምሪያ አስታዉቋል፡፡ህገ-መንግስዊ ሥርዓቱን ለማስከበር በወንጀልና በፍታብሔር ጉዳዮች በበጀት ዓመቱ ውጤታማ ሥራዎች መሠራታቸውን የደቡብ ወሎ ዞን ፍትህ መምሪያ ኃላፊ አቶ አብርሃም ሞላ ተናግረዋል፡፡3 ሺህ 247 የወንጀል መዛግብትን ፍትህ መምሪያው ለፍርድ ቤት አቅርቦ 1 ሺህ 773 የሚሆኑት ውሳኔ ያገኙ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1 ሺህ 655 የሚሆኑት ጥፋተኛ ሲሆኑ 118ቱ ደግሞ ነፃ ተብለዋል፡፡

የማስቀጣት ምጣኔ ከባለፈው ዓመት 2 በመቶ ጨምሯል፡፡ በሌላ በኩል በተከሳሽነት ደግሞ የማስቀጣት ምጣኔው ከዕቅዱ በተመሳሳይ 97 በመቶ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ ከሙስና ጋር በተያያዘ ከ20 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር በላይ መምሪያው ማዳን ችሏል፡፡

የገንዘብ መጠናቸው ከ56 ነጥብ 1 ሚሊዮን ብር በላይ የሆኑ እና 27 ሺህ 544 ካሬ ሜትር መሬት 240 የፍታብሄር መዛግብትን ለፍርድ ቤት በማቅረብ 102 መዛግብትን በማስቀጣት የማሸነፍ ምጣኔው ከዕቅዱ 98 በመቶ መድረሱን አቶ አብርሃም አንስተዋል፡፡ በዞን እና በወረዳ መንግስት ተከሶበት የነበረው 418 ሚሊዮን 682 ሺህ 484 ብር እንዲሁም 205 ሺህ 620 ካሬ ሜትር መሬት ፍትህ መምሪያው ተከራክሮ ማዳን እንደቻለ አቶ አብርሃም ተናግረዋል፡፡ይህም ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር ከ180 ሚሊዮን ብር በላይ ብልጫ መኖሩ ተመላክቷል፡፡

# የሲዳማ ክልል ሥነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድ ከሥነምግባር መከታተያ ዳይረክተሮች ጋር ዉይይት አካሄደ

የዉይይት መድረኩን በንግግር የከፈቱት የክልሉ ሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ወ/ሮ ዘላለም ለማ፣ ሙስና የህዝብና የመንግስት ሀብት ለታለመለት ዓላማ እንዳይዉል ትልቅ እንቅፋት ነዉ፤ ይህም ህዝብ ማግኘት ያለበትን ልማትና እድገት በማሳጣት ለከፋ ድህነትና ችግር የሚዳርግ አስከፊ ወንጀል ነዉ ስሉ ተናግረዋል።



ሙስና መንግስት በየዘርፉ የሚነሱ የህዝብ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚሰሩዋቸዉን የልማት እንቅስሴዎችን የሚያደናቅፍ ወንጀል ከመሆኑም በላይ ህዝብ በመንግስት ላይ ያለዉን አመኔታ በማሳጣት ለግጭት ይደርጋል ስሉም አያይዘው ገልፀዋል። ኮሚሽኑ በየደረጃ ከክልል እስከ ወረዳ ካሉ የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፍሰሮች ጋር በመቀናጀት ባደረገዉ የፀ-ረሙስና ትግል በሀገር ደረጃ የተሻለ አፈፃፀም ማስመዝገቡን አመላከተዋል።

የሙስና ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ የሚወሰድ የእርምት እርምጃ ህዝብንና መንግስትን ለተጨማሪ ክሳራ ይዳርጋል ያሉት ኮሚሽነር ዘላለም ወንጀሉ ከመፈፀሙ በፊት በሚሰሩ ስራዎች ላይ አትኩሮ መስራቱንና ከዚህ ባለፈ በወንጀል ወስጥ የተዘፈቁትን በህግ አግባብ እንድጠየቁ የማድረግ ስራ መሰራቱንም አያይዘው ተናግረዋል። ዛሬም ትግል የሚጠይቁ የሌብነት ተግባራት መኖራቸዉን የተደረጉ ጥናቶች ግኝት እንደሚያሳይ በማንሳት በተለይ በተቋማት ዉስጥ ያለጨረታና የገበያ ጥናት ሳይደረግ ግዢ መፈፀም እንድሁም በቅጥርና ዝዉዉር ዙሪያ የሚደረግ ግልፀኝነትና ፍትሐዊነት የጎደላቸው አሰራሮች መበራከታቸዉን ጠቁመዉ በዚህ ዙሪያም ትኩረት ሰጥተን ልንሰራ ይገባል ስሉ አሳስበዋል።

በሌላ በኩል ግልፀኝነትና ተጠያቂነት የጎደለዉ አሰራር ለሙስና በር እንደምከፍቱ ገልፀዉ ሀብት የማስመዝገብና የገቢ ምንጭን የማሳወቅ ስራ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እንድሰሩና የገቢ ምንጫቸዉ ያልታወቁ ሀብቶች ከተገኘም በህግ አግባብ እንዲጠየቁ የማድረግ ስራ ላይ አጽንኦት ተሰጥቶ ልሰራባቸዉ እንደሚገባም አክለዋል። የ2018 ዓ. ም ከኮሚሽኑ ለሥነ-ምግባር መከታተያ አፍሰሮች የሚወርድ ጠቋም እቅድ በአሰፋ ወርቅነህ አማካይነት ቀርቦ በቀረበዉ እቅድ መነሻነት ሁሉም በያለበት በአግባቡ አቅዶ በጥንካረ እንዲተገብሩና የተሻለ አፈፃፀም እንዲያስመዘግቡ የጋራ ስምምነት ላይ ተደርሶ ከመድረክም አቅጣጫ ተሰጥቶ መድረኩ ተጠቃሏል።



# በ2018 በጀት አመት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በትኩረት እንደሚሰራ ገለፀ፡-የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ በዋና መስሪያ ቤቱ ፣ በ17ቱ ቅርንጫፎችና በወረዳ ካሉ ከ7ሺህ በላይ ከሆኑ አመራሮችና ሰራተኞችጋር በመልካም አስተዳደር፣ በአግልግሎት አሰጣጥና በሌብነትና ብልሹ አሰራር ዙሪያ ውይይት አካሂዷል፡፡

በውይይቱ የቪዲዮ ገለፃ ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ሀላፊ አቶ ቢንያም ምክሩ በ2018 በጀት ዓመት ቢሮው በአገልግሎት አሰጣጥ መሰረታዊ ለውጥ በማምጣት የግብር ከፋዮች እርካታ ለማሻሻል በትኩረት ይሰራል ብለዋል፡፡

በተቋሙ የሚታዩ የሌብነት ፣ የብልሹ አሰራር ፣ የመልካም አስተዳደር እና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች ፍትህዊ የታክስ አሰባሰብ በተሟላ ደረጃ እንዳይዘረጋ እንቅፋት የሚፈጥሩ መሆናቸው ያነሱት ኃላፊው ችግሮቹን ለመቅረፍ ሁሉም የተቋሙ አመራርና ባለሙያ ሚናውን በአግባቡ ሊወጣ ይገባል ብለዋል፡፡

የተጠያቂነት ስርዓት ከማጠናከር አኳያም ከተመደቡበት የታክስ ሴንተር ውጪ ቫት ለግብር ከፋዮች በቋሚነት ሲያሳውቁ የነበሩ 115 ባለሙያዎችን እንዲሁም በየቅርንጫፉ ግብር ከፋዮች የሚጠበቅባቸው ግብር ሳይከፍሉ ክሊራንስ የሰጡ 16 ባለሙያዎች ተጠያቂ መደረጋቸውንም አንስተዋል፡ ፡ ቢሮው በበጀት ዓመቱ የአገልግሎት አሰጣጥና የመልካም አስተዳደር እንዲሁም የሌብነትና ብልሹ አሰራሮች በዘላቂነት ለመቅረፍ የሚያግዙ አሰራሮችና አደረጃጀቶች በጥናት



በመለየት ወደ ተግባር ማሸጋገሩን በመግለፅ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ እንዲደገፉ በውስጥ አቅምና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የለሙ ቴክኖሎጂዎች ወደ ተግባር እየተሸጋገሩ ናቸው ብለዋል፡፡

በ2018 በጀት ዓመት የግብር ከፋዩን እርካታ ለማሻሻል በትኩረትእየተሰራመሆኑንየገለፁትአቶቢኒያምየተጠያቂነት አሰራርን በማጠናከር የመልካም አስተዳደር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች በተሟላ ደረጃ ለመቅረፍ ይሰራል ብለዋል፡ ፡ ከዚህም በተጨማሪ በማዕከልም ሆነ በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች በሌብነትና ብልሹ ድርጊት ውስጥ የገቡ ብቻም ሳይሆን ለግብር ከፋዩ ተገቢውን ክብር የማሰጡ፣ ስራዎችን በጥናት በተለዩ ስታንዳርዶች የማይፈፅሙ፣ ለግብር ከፋዮች ተገቢውን አገልግሎት የማይሰጡ ጭምር ተጠያቂ ይሆናሉ ሲሉም ተናግረዋል፡፡ በመጨረሻም በማዕከል ቢሮና በ17ቱ ቅርንጫፎች ፅ/ቤቶች በመድረኩ ተሳታፊዎች በቀረበው ገለፃ መነሻነት ሰፊ ውይይት የደረጉ ሲሆን ከሌብንትና ብልሹ ድርጊቶች ጋር በተያያዘ በጥቂት ባለሙያዎች የተቋሙ ስም መጠልሸት ስለሌለበት የተጠያቂነት አሰራሩ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባልም ብለዋል፡፡ ከመልካም አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተመለከተም ለግብር ከፋዮች ተገቢውን አገልግሎት በመስጠት እንዲሁም የተዘረጉ አሰራሮች በአግባቡ በመተግበር የሌብነትና ብልሹ አሰራር ለመቅረፍ ኃላፊነታችንን እንወጣለን ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በተመሳሳይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ የአሰራር ግልጽነትን ለማስፈን፣ ሌብነትና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል እንዲሁም ፍትሐዊ የሆነ የቁጥጥር ስራ ለመስራት የቁጥጥር ስራው በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ማድረጉን አስታዉቋል ፡፡

# የስብዕና መገንቢያ ማዕከላቱ ወጣቶች ክህሎታቸውንና ምግባራቸዉን እንዲያዳብሩ አስችሏቸዋል



የስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ክህሎታቸውን ለማዳበርና ጊዜያቸውን አልባሌ ቦታ እንዳያሳልፉ እድል እየፈጠሩላቸው መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች ተናገሩ።

ተማሪዎች የክረምት እረፍት ጊዜያቸውን ከትምህርት ገበታ ውጭ ቢሆኑም አዳዲስ ነገሮችን እንዲመራምሩ እና በትምህርት ዓመቱ የማይቻሉ ይመስሏቸው የነበሩ አዳዲስ ችሎታዎችን እንዲማሩ አጋጣሚ ይሰጣል። ለአብነትም የሳይንስ ክበብ፣ የሒሳብ ውድድሮች፣ ስዕሎችን መሳል፣ የኪነ ጥበብ ትምህርቶች እና ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ተጠቃሽ ናቸው።

ኢዜአ ወጣቶች የክረምት የእረፍት ጊዜያቸው እንዴት እያሳለፉ እንደሚገኙ በከተማው በሚገኙ ወጣት የስብዕና መገንቢያ ማዕከላት በመገኘት አነጋግሯል።

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ አምስት የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከል ቁጥር 2 ያገኘናት ተማሪ ሰላም ደረጀ በእረፍት ጊዜዋ ለዲዛይንና ቅርጻ ቅርጽ አጋዥ የሚሆናትን በቂ የሙያ ስልጠናና ክህሎት እያገኘች መሆኗን አንስታለች፡፡

ወጣት ረድኤት ዳኛቸው በበኩሏ በእረፍት ጊዜዋ የአርት ስልጠና እየወሰደች እንደምትገኝ ጠቅሳ፤ በዚህም የትወና፣ የድርሰትና የስነ ጽሁፍ አጻጻፍ ስልቶች ላይ በቂ እውቀት በመቅሰም ላይ መሆኗን አስታውቃለች፡፡ በእረፍት ጊዜዋ የሜካፕ ሙያ ስልጠና እየወሰደች መሆኗን የተናገረችው ደግሞ 12ተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወስዳ ውጤት በመጠባበቅ ላይ የምትገኘው ወጣት እመቤት ጫሌ ናት፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት ወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከል ተጠቃሚ የሆነው ወጣት ዘሪሁን ጥላሁን በማዕከሉ መፅሐፍትን በማንበብ ጊዜውን እያሳለፈ መሆኑን ተናግሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በማዕከሉ የኮምፒዩተር፣ ጂም፣ ውዝዋዜ እና የተለያዩ የኪነ ጥበብ ስልጠናዎች እየተሰጡ እንደሚገኙም ጠቅሷል፡፡ በማዕከሉ የኮምፒዩተር ስልጠና የሚከታተሉት ወጣት ሰለሞን ወንዲፍራው እና የአብስራ ዘይኑ በበኩላቸው ስልጠናው የኮምፒዩተር አጠቃቀም ክህሎታችንን የሚያዳብርና በቀጣይ ለሚጠብቀን የኮምፒዩተር ትምህርት ዝግጁ የሚያደርገን ነው ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ በላይ ደጀን፤ ከተማ አስተዳደሩ ትኩረት ሰጥቶ ከሚሰራቸው ቁልፍ ተግባራት ውስጥ የወጣት ስብዕና ግንባታ ተቀዳሚ ተግባር ነው ብለዋል፡፡ በዚህም በከተማው በሁሉም ክፍለ ከተሞች በሚገኙ ወረዳዎች 114 የወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ተገንብተው 18 ዓይነት አገልግሎት በመስጠት ላይ እንደሚገኙ አስታውቀዋል፡፡ ይህም ወጣቶቹ ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ ከማስቻሉ ባለፈ ጊዜያቸውን አልባሌ ቦታ እንዳያባክኑ ከፍተኛ ሚና አለው ብለዋል፡፡

## የይዞታ ካርታ አዘጋጃለሁ በሚል 50ሺህ ብር ጉቦ የተቀበለ የይዞታ ማረጋገጥና ምዝገባ ባለሙያ በቁጥጥር ስር ዋለ

የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመው ሐምሌ 30 ቀን 2017 ዓ/ም ከቀኑ 5:00 ሠዓት በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 7 ልዩ ቦታው ቤተል አካባቢ መሆኑን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን አስታውቋል::

ተከሳሽ ሳምሶን ፍስሀ በክ/ከተማው የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት የይዞታ ማረጋገጥና ምዝገባ ባለሙያ ሲሆን የግል ተበዳይ የሆኑት አቶ ባይሳ ሚልኬሳ በፍርድ ቤት በነበራቸው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ በማሸነፋቸውና ሲከራከሩበት የነበረው መሬት 397.58 ካሬ የይዞታ ካርታ እንዲዘጋጅላቸው በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ተሠጥቷል::

ግለሰቡም የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ይዘው ወደ ጽ/ቤቱ ባለሙያ በመቅረብ ካርታው እንዲሠራላቸው ቢያደርጉም ባለሙያው ግን የይዞታ ካርታውን 342 ካሬ አድርጎ በመስራቱ ፍርድ ቤቱ እንዲሰራ ያዘዘው 397.58 ካሬ ባለመሠራቱ ተስተካክሎ እንዲሠራ ተለዋጭ ትዕዛዝም ይሠጣል::

የግል ተበዳይ ይህንን ተለዋጭ ትዕዛዝ በመያዝ ወደ ጽ/ቤቱ ሲመለሱ በተከሳሽ በኩል ካርታውን ለማስተካከል 50ሺህ ብር እንዲከፍሉ በመጠየቃቸው ለፖሊስ በሠጡት ጥቆማ ገንዘቡን ሲቀበል እጅ ከፍንጅ በቁጥጥር ስር ሊውል ችሏል:: ፖሊስ በተጠርጣሪው ላይ ተገቢውን የምርመራ ተግባር እያከናወነ እንደሚገኝ ገልጿል::

## የሥነምግባር ጥሰት በፈፀሙ 92 አመራርና ሰራተኞች ላይ እርምጃ ተወሰደ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በ2017 በጀት ዓመት 12 ወራት ተቋሙ ተግባራዊ ባደረገው ዲጂታል የሙስና ተግባር መጠቆሚያ ሞባይል አፕሊኬሽን እና በሌሎች አማራጮች ከቀረቡ 147 ጥቆማዎች 92 አመራርና ሰራተኞች ጥፋተኛ መሆናቸው ተረጋግጦ እርምጃ የተወሰደ ሲሆን የቀሪዎቹ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

ተቋሙ ተግባራዊ ባደረገው የሙስና ጥቆማ ማቅረቢያ እና በሌሎች አማራጮች በቀረቡት ጥቆማዎች መሰረት እርምጃ ከተወሰደባቸው ሰራተኞች መካከል 11 የፅሁፍ፣ 63 የደመወዝ፣ 4 ስንብት፣ 5 ከቦታ ማንሳት እንዲሁም 9 ነፃ የተባሉ በድምሩ በ92 አመራርና ሰራተኞች ላይ እርምጃ ተወስዷል፡፡ ተግባራዊ በተደረገው የዲጂታል ሙስና ጥቆማ መቀበያ አፕልኬሽን እና በሌሎች አማራጮች 364 ጥቆማዎች ቀርበው በ311 ጥቆማዎችን ማጣራት ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ የብልሹ አሰራር ጥቆማ ከቀረበባቸው የስራ ሂደቶች መካከል የአዲስ ኃይል ጥያቄ፣ ገንዘብ ስብሰባና ቆጣሪ ንባብ፣ የኃይል መቆራረጥና ጥገና፣ የሰው ሃብት አስተዳደር፣ ከንብረት አያያዝና አጠቃቀም፣የግዥ ሥራዎችና ሌሎች ልዩ ልዩ ጉዳዮች ይገኙበታል፡፡

በ2017 ዓ.ም ብቻ የቀረቡ ጥቆማዎች ብዛት ባለፉት 3 ዓመታት ከቀረቡት አጠቃላይ ጥቆማዎች ድምር ጋር ተቀራራቢ ሲሆን ይህም የዲጂታል መተግበሪያው/

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት
Ethiopian Electric Utility

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀን የሚዘጋጅ ጋዜጣ

ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች EARS**

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ሞባይል 0935947533
0953222299
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስኣፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

**NCRS**


# ርዕሰ -አንቀፅ

## በመንግስት መ/ቤቶች፣በልማት ድርጅቶችና ህዝባዊ ተቋማት ያሉ መከታተያ ክፍሎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከልና መታገል አለባቸዉ

የሙስና ምንጭ ከሆኑት አንዱ ብልሹ አሠራር ነው። ብልሹ አሠራር ደግሞ የሥነ ምግባር ጉድለት ውጤት ነው። የሥነምግባር ጉድለት ከሞራል ዝቅጠት ጋር የሚያያዝ ነው።

በመሆኑም ሙስና ከየትኛውም ወንጀል በላቀ መልኩ ውስብስብና አደገኛ በኔትዎርክ የሚሠራ ፣ላይ ታችና የጎን ቁርኝት ያለው፣ በሙስና የሚሳተፉት አብዛኞቹ የተማሩ፣ በመንግሥትና በሌሎች ድርጅት የሥልጣንና ከሥልጣን ጋር ተያያዥ ባለው ጉዳዮች ልምድ ያላቸው፣ በድርጊቱ እንዴት ከተጠያቅነት ማምለጥ በሚችሉበት የረቀቀ አሠራር መከወን የሚችሉ፣ ለወንጀላቸው ሽፋን ሊሠጧቸው የሚችሉ ማንኛውም ወሳኝ የውጭና ውስጥ አካላት ጋር ግንኙነት ያላቸው አካላት የሚሠራ አደገኛ ወንጀል ነው።

ስለሆነም ትግሉ በያዝ ለቀቅ፣ደብዘዝ ደመቅ አካሄድ ውጤታማ መሆን አይችልም።እውነቱን ለመናገር በተቋማት ውስጥ የሚሠሩ ሙስናና ብልሹ አሠራር ከተቋሙ ባለ ሥልጣን ዕይታ ውጭ አይሆንም።

ስለዚህ ሙስናንና ብልሹ አሠራርን ለመዋጋት በተቋማት ውስጥ የተዋቀሩ ወይም የተደራጁ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ተልዕኮአቸውን በአግባቡ መወጣት አለባቸዉ፡፡

# ቆይታ



# በ2017 በጀት ዓመት በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ማዳን ተችሏል:- ምክትል ኮሚሽነር እሸቴ አስፋው

የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ተልዕኮውን ለመወጣት የተለያዩ መንገዶችን/አማራጮችን በመጠቀም ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራዎችን ከሚሰራባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሲሆን በዚህም በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ የሚዘጋጅ የዲጅታል ጋዜጣ በማዘጋጀት ለማህበረሰቡ ያደርሳል፡፡ ጋዜጣው ከያዛቸው አምዕዶች ውስጥ ደግሞ ቆይታ አንዱ ነው፡፡ በዚህ ዝግጅት ቆይታ ያደረገው ከፌደራል ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የኮሚሽኑ የሙስና መከላከል፣ ጥናትና ክትትል ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር እሸቴ አስፋው የዘርፉን የ2017 በጀት ዓመት የእቅድ አፈጻጸምና የ2018 በጀት ዓመት እቅድ አስመልክቶ የተዘጋጀ መጠይቅ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:- በመጀመሪያ ደረጃ በሙስና መከላከል ዘርፍ ያሉት የሥራ ክፍሎች ምን ምን ናቸው? ተግባራቸውን ጨምሮ ቢገልፁልን?*

**ክቡር ም/ኮሚሽነር እሸቴ አስፋው:-** በሙስና መከላከል ዘርፍ ሦስት መሠረታዊ የሥራ ክፍሎች አሉ፡፡ እነሱም:- የሙስና መከላከል ጥናትና ክትትል፣ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል፣ የሀብት ምዝገባና የጥቅም ግጭት ማስወገድ ናቸው፡፡

የሙስና መከላከል ጥናትና ክትትል ክፍል በተመለከተ በፌዴራል ደረጃ ያሉ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች፣ ተጠሪ ተቋማትና ሌሎች ሕዝባዊ ድርጅቶች የአሠራር ሥርዓታቸውን ያጠናል ይገመግማል፡፡ በአዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያና የሕግ ማዕቀፎች መሠረት ሙስናና ብልሹ አሠራሮችን መከላከል የሚችሉበትን ሁኔታ ይፈትሻል፡፡ ይህ ምርመራ በሳይንሳዊ ዘዴ ይከናወናል፡፡ የጥናቱ ግኝቶችንና ምክረ ሐሳቦችን ያቀርባል፣ በተለይ የአመራሩ ሚና በሙስና መከላከል ላይ እንዲያተኩር ምክረ ሀሳቦችን ያስቀምጣል፡፡ በዘርፉ 25 ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት በዋናነት ይገመገማሉ፡፡ እነዚህም የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት፣ የፍርድ ቤት ዘርፍ፣ የአስተዳደር ዘርፍና ሌሎች የሕዝባዊ ድርጅቶች ያካትታሉ፡፡

የአስቸኳይ ሙስና መከላከል በአዋጅ ቁጥር 1236/2013፣ አንቀጽ 7 ንኡስ አንቀጽ 4 መሠረት፣ ይህ ክፍል ሙስና ወይም ብልሹ አሠራር ስለመፈጸሙ ጥርጣሬ ሲኖር ወይም ጥቆማ ሲደርስ አስቸኳይ ምርመራ ያካሂዳል፡፡ የሙስና ድርጊቶችን ከመፈጸሙ በፊት መከላከል፣ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል፣ እንዲሁም ወንጀል ሆኖ ሲገኝ ለሕግ አስፈጻሚ አካላት ማስተላለፍ ያካትታል፡፡

ሌላዉ የሀብት ምዝገባና የጥቅም ግጭትማስወገድ ሲሆን ይህ ክፍል በአዋጅ መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ የልማት ድርጅቶችና ሕዝባዊ ድርጅቶች ሠራተኞች የሀብት ምዝገባ እንዲያካሂዱ ያስፈልጋል፡፡ የተለያየ አይነት የሀብት ምዝገባዎች አሉ፡፡ እነሱም:- አዲስ ሀብት ምዝገባ (አዲስ ተቀጣሪ ሠራተኞች የሀብታቸውን መዝግቦ ማቅረብ)፣ እድሳት (ከሁለት ዓመት በኋላ ተመዝጋቢው ሀብቱን እንደገና የሚገልጽበት ሂደት)፣ የማቋረጥ እና መውጫ (ሠራተኛው ከተቋሙ ሲለቅ በጥሮታ፣ በስንብት ወይም በሌላ ምክንያት የሚደረግ ምዝገባ ነው፡፡

*ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:- በ2017 በጀት ዓመት የሙስና መከላከል፣ ጥናትና ክትትል ዘርፍ የእቅድ አፈጻጸም ምን ይመስል ነበር? ዋና ዋና ውጤቶችን እና ፈተናዎችን ቢያብራሩልን?*



**ክቡር ም/ኮሚሽነር እሸቴ አስፋው:-** በ2017 በጀት ዓመት የሙስናና ብልሹ አሠራር መከላከል ዘርፍ የእቅድ አፈጻጸም በአጠቃላይ ጥሩ ደረጃ ላይ ነበር ተብሎ ተገምግሟል፡፡ ዘርፉ ተልዕኮዎቹንና ተግባሮቹን በተቀመጡት ቁልፍ የብቃት መለኪያዎች (KPI) መሠረት ከ100% በላይ ማሳካት ችሏል፡፡ ይህም የተሳካና ርብርብ የተደረገበት ዓመት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ዋና ውጤቶች፡ በጥናት ዘርፍ:- በዓመቱ ወደ አስር የሚሆኑ ዘርፎች ላይ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ እነዚህም የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ሥርዓት፣ የጉምሩክ አስተዳደርና ኮንትሮባንድ፣ የመንግሥት ግዥ አስተዳደር ግልጽነት፣ የውጭ ሥራ ስምሪት፣ የመንግሥት የመስኖና የመንገድ ፕሮጀክቶች፣ የኢንቨስትመንት መሬት፣ የውጭ ኢንቨስትመንትና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ጉዳዮችን ያካትታሉ፡፡

ኮሚሽኑ ሀብት ምዝገባ በዲጂታል ሥርዓት የጀመረው የሀብት ምዝገባ ስርዓት(ኢርስ) በ2017 ወደ መጨረሻ ላይ የተጀመረ ቢሆንም 2,951 አዲስ አስመዝጋቢዎችና 8,679 እድሳት አስመዝጋቢዎች፣ በጠቅላላ 11,630 አስመዝጋቢዎችን ያካተተ ሲሆን፣ በተለይ ትኩረት የተደረገበት የተቋም ሃላፊዎችና የዲስክ መሪዎች በምዝገባው ሀብታቸውን ለማስመዝገብ ተሳትፈዋል፡፡

ፈተናዎች ተብለዉ ከተጠቀሱት ዉስጥ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ ሙስናና ብልሹ አሠራሮችን ሙሉ በሙሉ ነጻ ለማድረግ ሰፊ ሥራ ይጠበቃል፣አንዳንድ ተቋማት ለሥራው ትኩረት አለመስጠትና የባለቤትነት ስሜት መጓደል፣ የሕዝብ ንቅናቄ ለመፍጠር የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ሥራዎች በበጀት ውስንነት ምክንያት በተፈለገው ደረጃ መከናወን አለመቻላቸው እና የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት ሰፊ ሥራ ያስፈልጋል፡፡

*ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:-በ2017 በጀት ዓመት ሙስናን በአስቸኳይ ሙስና መከላከል የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት እና በዚህ የዳኑ የሀብት መጠኖች ቢገለጹልን?*

**ክቡር ም/ኮሚሽነር እሸቴ አስፋው:-** በ2017 በጀት ዓመት በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራዎች ላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ትልቅ ንቅናቄ ተካሂዷል፡፡ በፌዴራል ደረጃ 24 የሙስና መከላከል ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚህ ወደ 2.5 ቢሊዮን ብር ሀብት ማዳን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም፣ 270,078.15 ካሬ ሜትር የከተማና የገጠር ኢንቨስትመንት መሬት ተመልሷል፡፡ እነዚህ ሥራዎች በጥቆማ መሠረት በፌዴራል፣ በክልልና በከተማ አስተዳደሮች በመተባበር ተከናውነዋል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ኮንፈረንስ ተካሂዶ፣ ከክልሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ተደርጓል፡፡ ይህ ሥራ ልምድና እውቀት የተገኘበትና ለቀጣይ መነሻ ይሆናል፡፡

*ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:- በዲጂታል ሀብት ምዝገባ ሥራዎች ምን ያህል አስመዝጋቢዎች ተመዝግበዋል? የሀብት ምዝገባ ዓላማዎችንና ጠቀሜታዎችን በዝርዝር ቢያብራሩልን?*

**ክቡር ም/ኮሚሽነር እሸቴ አስፋው:-** በ2017 በጀት ዓመት የዲጂታል ሀብት ምዝገባ (EARS) መጨረሻ ላይ ተጀምሮ 2,951 አዲስ አስመዝጋቢዎችና 8,679 እድሳት አስመዝጋቢዎች፣ በጠቅላላ 11,630 አስመዝጋቢዎች ተመዝግበዋል፡፡ በፌዴራል ደረጃ በተለይ የተቋም ሃላፊዎች፣ የዲስክ መሪዎችና ቡድን መሪዎች በምዝገባው ተሳትፈዋል፡፡ በክልሎችም በሺዎች የሚቆጠሩ ምዝገባዎች ተካሂደዋል፡፡ ለ2018 በጀት ዓመት ወደ 45,000 አስመዝጋቢዎች (10,000 አዲስና 35,000 እድሳት) ለማስመዝገብ ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል፡፡

የሀብት ምዝገባ ዓላማዎችና ጠቀሜታዎች፡ የሙስና መከላከል፣ የጥቅም ግጭቶችን መቆጣጠር፣ የተመዘገበው ሀብት ትክክለኛነት ማረጋገጥ እና የተመዝጋቢዎችን ሀብት ግልጽነት መጠበቅ እንዲሁም ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ሲገኝ ተጠያቂ ለማድረግ ነው፡፡

*ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:- የሙስና መከላከል ዘርፍ የ2018 በጀት ዓመት እቅድ ምን ይመስላል? የእቅዱ መነሻዎች፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች፣ ፈተናዎች እና የተዘጋጁ ቅድመ ዝግጅቶች ምን እንደሆኑ በዝርዝር ቢገልጹልን?*

**ክቡር ም/ኮሚሽነር እሸቴ አስፋው:-** የ2018 በጀት ዓመት እቅድ በተመለከተ ዘርፉ የተለያዩ መነሻዎችን መሠረት ያደረገ ሲሆን የመካከለኛ ዘመን እቅድ ግምገማ፣ የመካከለኛ ዘመን እቅድ አፈጻጸም ማጠቃለያ ጊዜ ስለሆነ፣ ይህን ታሳቢ በማድረግ እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ የሀብትና የሰው ሀይል አቅም፡ ያለውን ሀብትና ሰው ሀይል በተሻለ ሁኔታ በመጠቀም ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እቅዱ ተዘጋጅቷል፡፡ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች፡ የሙስና መከላከል ትኩረት፡ ሙስና ከመፈጸሙ በፊት መከላከል ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡ ይህም የሕዝብ ድምጽ በማሰማትና በመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የመስክ ምልከታና የጥናት ጥናቶችን ያካትታል፡፡

የጥናት ሥራዎች፡ በ26 ዘርፎች ላይ የሥነ ምግባር መከላከያ ክፍሎች ጥናቶችን እንዲያካሂዱ ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል፡፡ ኮሚሽኑ በተለይ በስምንት ወሳኝ ዘርፎች ላይ ጥናቶችን ያካሂዳል፡፡

የሀብት ምዝገባ፡ በዲጂታል ሥርዓት ወደ 45,000 አስመዝጋቢዎች (10,000 አዲስና 35,000 እድሳት) ለማስመዝገብ እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

ነገር ግን ያሉ ችግሮችን ማለትም የሕዝብ ንቅናቄ እጥረትና የባለቤትነት ስሜት መጓደል፣ በጀት ውስንነት ምክንያት የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ሥራዎች መገደብ፣ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት ያለው ተግዳሮቶችን በመፍታት የሰው ሀይልና ሀብት አቅም ማጠናከር፤ በሁሉም ዘርፎች የሥነ ምግባር መከላከያ ክፍሎችን ማጠናከር፤ በክልሎች ያለውን የሙስና መከላከል ሥራ በማጠናከር ሁሉን አቀፍ ቅንጅት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

*ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:- በመጨረሻም ለህዝብ ወይም ለባለድርሻ አካላት የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?*

**ክቡር ም/ኮሚሽነር እሸቴ አስፋው:-** ሙስናና ብልሹ አሠራር በአለም አቀፍ ደረጃ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና የፀጥታ ስጋት ነው፡፡ ሀገራችን በፈጣን እድገት ለውጥ ምህዳር ውስጥ ገብታለች፡፡ ይህን ለማስቀጠልና ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር፣ የበለጸገችና የብልጽግና ተምሳሌት የሆነች ሀገር ለመገንባት ሙስናና ብልሹ አሠራር ነጻ የሆነ ልማት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ለማሳካት የሲቪክ ማኅበራት፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የሕግ አስከባሪ አካላትና አጠቃላይ ማኅበረሰቡ የድርሻቸውን መጫወት አለባቸው፡፡ ሙስናን መሸከም የማይችል ማኅበረሰብ ለመፍጠር የሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብና ጥረት ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል፣ ሙስና የሚፈጸመው በሙሰኛው ብቻ ሳይሆን፣ ሰጪ በሌለበት ተቀባይ አይኖርም፣ስለዚህ ሕብረተሰቡ መብቱን በገንዘብ ሳይገዛ ለመብቱ መታገል አለበት፡፡ ሚዲያውና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የራሳቸውን ሚና በመወጣት የበለጸገችና የብልጽግና ተምሳሌት የሆነች ኢትዮጵያን ለመፍጠር አስተዋጽኦ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ይህን ለማሳካት የሁሉም ድጋፍና ቅንጅት ያስፈልጋል የሚል አደራ እላለሁ፡፡

**አመሰግናለሁ!**

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

ይህ አምድ በዋናነት ትኩረት የሚያደረገው ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ በማስገኘት ወይም ለሌላ ሰው በማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት በማድረስ በተሰጠዉ ኃላፊነት ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም በማስገኘት የተሰጠዉን ስልጣን ወይም የህዝብ አደራ ያላአግባብ የተገለገለ፤ ወይም ለሌላ ሰው ያስገኘ ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ ለመንግስት ወይም ለህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ፤ ወይም በአግባቡ ለተፈጸመ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግሰት ልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ስራ የማይገባ ጥቅም ለማንኛውም ሰዉ የሰጠ ወይም ከማንኛዉም የመንግስት ወይም ህዝባዉ ድርጅት ሰራተኛ የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ፈጻሚነት ተጠያቂ በመሆን በምርመራ የሙስና ወንጀል ፈፅመው የተገኙ አካላት መረጃዎችን ለአንባቢያን ተደራሽ የምዳረግበት ነው።

በዚሁ መሰረት የመድኃኒት ግዥ ጥያቄ እንደቀረበ በማስመሰል በሀሰት ሰነድ ግዥ ሊፈፅም የነበረ ግለሰብ በፅኑ እስራት ተቀጣ

አቶ ሱራ ያዕቆብ የተባለ ግለሰብ መጋቢት30/1 ቀን 2017 በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ወለጋ ዞን ጊምቢ ወረዳ የወንጀል ድርጊቱን ፈፅሟል። ወዴሳ ዋርካ ተብሎ በሚጠራ የመንግስት ጤና ተቋም ስም የመድኃኒት ግዥ ጥያቄ እንደቀረበ በማስመሰል በሀሰት ሰነድ 164 ሺህ 881ብር የሚያወጡ 106 አይነት መድኃኒቶች በአገልግሎቱ ነቀምቴ ቅርንጫፍ በአካል በመገኘት ግዥ ለመፈፀም ሲሞክር የስራ ክፍሉ ባለሙያዎች በመጠርጠር ለፖሊስ አመልክተዉ ግለሰቡ በዕለቱ ቢሰወርም በፖሊስ አባላት ብርቱ ክትትል ግንቦት 15 ቀን 2017ዓ.ም ከተደበቀበት ሐሩ ወረዳ በህግ ቁጥጥር ስር መዋሉ ገልጿል፡፡

ወንጀለኛዉ በምስራቅ ወለጋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶበት በሰዉ እና በሰነድ ማስረጃዎች ወንጀሉን መፈፀሙ ተረጋግጦ ሀምሌ 15 ቀን 2017ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ፍርድ ቤቱ በአስራ አራት አመት ፅኑ እስራት እንደተፈረደበት ተገልጿል፡፡

በሌላ ዜና ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ስራ አስፈፃሚ የዕጅ መንሻ በማቅረብ የተጠረጠረው ቻይናዊ ተከሰሰ ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ስራ አስፈፃሚ 'ጉዳዬ በአፋጣኝ እንዲፈፀምልኝ' በማለት የዕጅ መንሻ በማቅረብ የተጠረጠረ ቻይናዊ ክስ ተመሠረተበት፡፡

ክሱ የተመሰረተው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ሁለተኛ የሙስና ወንጀሎች ችሎት ነው።

ተከሳሹ ሊ ሆንግ ኩዌ የተባለ ቻይናዊ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 25 (5) ላይ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ነው ክሱ የተመሠረተበት፡፡

የክሱ ዝርዝር እንደሚያስረዳው ተከሳሹ ዳ ቻንግ ኤሌክትሪክ ፓወር ማኑፋክቸሪንግ ኃ/የተ/ የግ/ማህበር የተባለ ድርጅት ባለቤት ሆኖ ሲሰራ በሐምሌ 18 ቀን 2017 ዓ.ም ከቀኑ 9 ሰዓት አካባቢ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና መስሪያ ቤት በአካል በመቅረብ ድርጅቱ አዲስ የትራንስፎርመር አምራች መሆኑን በመጥቀስ የአምራችነት ማረጋገጫ ፍቃድ እንዲሰጠው ላቀረበው ጥያቄ በአፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጠው ለተቋሙ ዋና ስራ አስፈጻሚ ለሆኑት 1ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር 1 ሺህ የአሜሪካ ዶላር በዕለቱ በነበረው የምንዛሪ ተመን 133 ሺህ 356.6 ብር ስጦታ ያቀረበ በመሆኑ በፈጸመው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት የሙስና ወንጀል ተከሷል፡፡

ተከሳሹ ፍርድ ቤት ቀርቦ ክሱ የተነበበለት ሲሆን ለጥቅምት 8 ቀን 2018 ዓም ቀጠሮ ተሰጥቶታል

በተመሳሳይ ተማሪዎችን የባንክ ሂሳብ በማስከፈት በወንጀል የተገኘ ገንዘብን አዘዋውረዋል የተባሉ 9 ግለሰቦች ተከሰሱ ሁለት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎችን የባንክ ሂሳብ በማስከፈት በወንጀል የተገኘ ገንዘብን አዘዋውረዋል የተባሉ ዘጠኝ ግለሰቦች ተከሰሱ።

ክሱን የመሰረተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ የሙስና ጉዳዮች ችሎት ነዉ፡፡ ተከሳሾቹ አቶ ዳዊት አያሌው፣ አቶ ሙየስር አህመድ፣ አቶ ዳንኤል ኪዱ እና አቶ ቴዎድሮስ ታደሰ ጨምሮ ዘጠኝ ግለሰቦች ላይ ዐቃቤ ሕግ ሁለት ክሶችን አቅርቧል።

በአንደኛ ክስ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉ ተከሳሾች የማይገባቸውን ብልጽግና ለራሳቸው ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ፣ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከፋይነት እና በመላ ሀሳባቸውና ድርጊታቸው በወንጀል ድርጊቱ ውስጥ ተካፋይ ሆነዋል። በዚህም 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች የ11ኛ ክፍል ተማሪ የሆኑትን 2ኛ እና 3ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ተማሪ ሳሙኤል ምትኩ እና ተማሪ ሳሙኤል አስፈራውን በአንድ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 500 ብር እንደሚከፈላቸው በመግለጽ በስማቸው የባንክ ሂሳብ እና የሞባይል ባንክ አገልግሎት በማስከፈትና የምስጢር ቁጥር እንዲሰጧቸው አግባብተዋቸዋል።

ተማሪዎቹ የከፈቷቸው የባንክ ሂሳቦች እና የሞባይል ባንክ አገልግሎት ምንም ችግር እንደማያመጣባቸው አሳሳች ቃል በመናገር ምስክሮቹ እምነት እንዲያሳድሩ በማታለል እና የሲም ካርዶችን በመስጠት፣ 2ኛ እና 3ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች በአቢሲኒያ እና ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች በመቅረብ በምስክሮቹ ስም የተከፈቱትን የባንክ ሂሳቦች ቁጥርን እና በሂሳቦቹ ላይ የተመዘገቡትን የሞባይል ባንክ አገልግሎት የሚስጥር ቁጥሮችን 1 ሺህ 500 ብር በመክፈል ምስክሮቹን አታለው ተቀብለዋል።

ከዚህም በኋላ የባንክ ሂሳብ ቁጥሮቹን፣ የሞባይል አገልግሎት የተመዘገበባቸውን ሲም ካርዶች እና በሲም ካርዶቹ የተመዘገቡትን የምባይል አገልግሎት የሚስጥር ቁጥሮቹን ለ3ኛ ተከሳሽ በመስጠት፣ 3ኛ ተከሳሽም የባንክ ሂሳብ ቁጥር፣ የሞባይል ባንክ አገልግሎት የሚስጥር ቁጥር ዮኒ በሚል ስም በከፈተው የዋትስአፕ አካውንት ወደ 4ኛ ተከሳሽ ልኳል።

4ኛ ተከሳሽ ከ1ኛ ዐቃቤ ህግ ምስክር አቶ ሰለሞን ተካ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክተንቀሳቃሽ የሂሳብ ቁጥር ላይ በቼክ የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብ ቼኩን ምስክሩ መስጠታቸውን ለማረጋገጥ የሚደወልበትን የሞባይል ስልክ ቁጥር ያልተያዘው አባሪያቸው ወደ ኢትዮ-ቴሌኮም ምስራቅ አዲስ አበባ ዞን ናፑ የፍራንቻይዝ የሽያጭ ቢሮ በመቅረብ በአቶ ሰለሞን ተካ ስም የተዘጋጀ ሀሰተኛ የመንጃ ፈቃድ በማቅረብ ምትክ ሲም ካርድ እንዲወስድ በማድረግ 4ኛ ተከሳሽ ሲም ካርዱን በመቀበል፣ ከ1ኛ ዐቃቤ ሕግ ምስክር አቶ ሰለሞን ተካ የአቢሲኒያ ባንክ የቁጠባ ሂሳብ ቁጥር ላይ ምትክ የሲም ካርዱን በመጠቀም በሞባይል ባንክ አገልግሎት በ2ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሳሙኤል ምትኩ ስም ወደ ተከፈተው የአቢሲንያ ባንክ የሂሳብ ቁጥር 99 ሺህ አስተላልፏል።

5ኛ ተከሳሽ አቶ ሰለሞን ተካ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከተረከቡት ተንቀሳቃሽ የሂሳብ ቁጥር ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ቼክ አቶ ሰለሞን ተካ ጽፈውና ፈርመው የሰጡት በማስመሰል 5ኛ ተከሳሽ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጎሮ አደባባይ ቅርንጫፍ ቀርቦ 2 ሚሊየን 650 ሺህ ብር ለክፍያ ሲያቀርብ የቅርንጫፍ ባንኩ ሰራተኞች ቼኩን አቶ ሰለሞን ተካ በትክክል ፈርመው መስጠታቸውን ለማረጋገጥ በሂሳቡ ላይ ወደ ተመዘገበው እና 4ኛ ተከሳሽ ባልተያዘው አባሪው አማካኝነት ምትክ ሲም በማውጣት ይዞት ወደ ነበረው የሞባይል ስልክ ቁጥር ሲደውሉ 4ኛ ተከሳሽ እራሱን የሂሳቡ ባለቤት በማስመሰል ክፍያው እንዲፈጸም ማረጋገጫ ሰጥቷል።

የባንኩ ሰራተኞች የሂሳቡ ባለቤት ማረጋገጫውን እንደሰጡ የወሰዱትን የተሳሳተ እምነት በመጠቀም ቼኩ ተመንዝሮ ወደ 5ኛ ተከሳሽ የንግድ ባንክ የሂሳብ ቁጥር 2 ሚሊየን 380 ሺህ 729 ብር ከ92 ሳንቲም እንዲተላለፍለት በማድረግ፤ በተማሪዋቹ ስም በተከፈቱ አካዉንቶች የገቡ ገንዘቦችን 3ኛ ተከሳሽ በሞባይል ባንኪንግ ወደ ተለያዩ ግለሰቦች የባንክ ሂሳብ ቁጥርና የሞባይል ባንክ አገልግሎት ወደ ተመዘገቡ የስልክ ቁጥሮች አስተላልፏል።

በአጠቃላይ ከ1ኛ እስከ 5ኛ የተጠቀሱት ተከሳሾች የማታለል የሙስና ወንጀል ድርጊታቸው በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ከ1ኛ ዐቃቤ ሕግ ምስክር አቶ ሰለሞን ተካ የአብሲኒያ ባንክ የቁጠባ ሂሳብ ቁጥር ላይ 99 ሺህ፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሂሳብ ቁጥር 2 ሚሊየን 650 ሺህ ብር በድምሩ 2 ሚሊየን 749 ሺህ ብር ተቀንሶ ወጪ እንዲሆን በማድረግ በፈጸሙት ድርጊት በከባድ አታላይነት የሙስና ወንጀል ተከሰዋል፡ ፡

በ2ኛ ክስ ደግሞ በ2ኛ እንዲሁም ከ6ኛ እስከ 9ኛ የተጠቀሱት ተከሳሾች ላይ የቀረበ ሲሆን ተከሳሾች ከላይ በ1ኛ ክስ በተጠቀሰው ከአቶ ሰለሞን ተካ ተንቀሳቃሽ የሂሳብ ቁጥር ላይ 2 ሚሊየን 650 ሺህ ብር ተቀንሶ ወደ 5ኛ ተከሳሽ የንግድ ባንክ የሂሳብ ቁጥር ከተላለፈ የወንጀል ፍሬ ከሆነ ገንዘብ ላይ ተቀንሶ ወደ ሂሳባቸው የገባውን ገንዘብ ህገ-ወጥ አመጣጥ ለመሰወር ወደ ሌሎች ግለሰቦች በማስተላለፋቸው በፈጸሙት የወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ በማቅረብ ወንጀል ተከሰዋል፡፡

## ይጠቁሙ!




**ለኤሌክትሪክ ጉዳይ ሙስና ስትጠየቁ በዚህ ጠቁሙን ሲል የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አሳውቋል፡፡ ከስነ-ምግባር ጥሰቶች ጋር የሚገናኙ ችግሮችን ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችል መተግበሪያ /አፕሊኬሽን/ በስራ ላይ አውሏል፡፡**

**የሞባይል መተግበሪያው ተቋሙ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ማዕከላት በሚስተናገዱበት ወቅት ለሚገጥማቸው ከብልሹ አሰራር ጋር የተያያዙ ችግሮች በቀላሉ ጥቆማ እንዲያቀርቡ ለማድረግ የሚያስችል ነው፡፡**

**መተግበሪያው በሁለት ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ እና እንግሊዘኛ ቋንቋዎች የተዘጋጀ ሲሆን በቀጣይም ለኤሌክትሪክ ጉዳይ ሙስና ስትጠየቁ በዚህ ጠቁሙን ሲል የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አሳውቋል፡፡ ከስነ-ምግባር ጥሰቶች ጋር የሚገናኙ ችግሮችን ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችል መተግበሪያ /አፕሊኬሽን/ በስራ ላይ አውሏል፡፡**

**የሞባይል መተግበሪያው ተቋሙ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ማዕከላት በሚስተናገዱበት ወቅት ለሚገጥማቸው ከብልሹ አሰራር ጋር የተያያዙ ችግሮች በቀላሉ ጥቆማ እንዲያቀርቡ ለማድረግ የሚያስችል ነው፡፡**

**መተግበሪያው በሁለት ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ እና እንግሊዘኛ ቋንቋዎች የተዘጋጀ ሲሆን በቀጣይም በሌሎች ተጨማሪ ቋንቋዎች አገልግሎት መስጠት እንዲችል ለማድረግ እየተሰራ ነው፡፡ የጥቆማ ማቅረቢያ መተግበሪያውን ብሮዘር ላይ" https://eeuethics.et" ብላችሁ በመግባት እና በማውረድ አልያም እዛው ላይ ጥቆማቸውን ወይም ቅሬታችሁን ሞልታችሁ መላክ ትችላላችሁ፡፡ የመተግበሪያው የአገልግሎት አሰጣጡን ፍትሃዊ በማድረግ የደንበኞችን እርካታ ለማሳደግ የሚረዳ በመሆኑ በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የብልሹ አሰራር ጥቆማዎችን እንድትሰጡ እንገልጻለን፡፡**

# ኪነ-ጥበብ

ባለብዙ ወዳጅ

## ባለብዙ ወዳጅ

ባለብዙ ወዳጅ ሁሉን በይ ቀበኛ፣
በድብቅ የሚጓዝ ሁሉ መንገደኛ፣
በሥራ ተግባሩ የሀገር ጠሰኛ፣
ይህን ስዉር ወዳጅ ይበጅለት ዳኛ፡፡

ሥሩ የረዘመ ስራዉ የጠመመ፣
መጥፎዉን ተግባሪ ጥሩን ያደከመ፣
ፍትህን አጓሎ ሚዛን ያጣመመ፣
መድሃኒትን ሽሮ መርዝን የቀመመ፣
እርሱ ነዉ ያጠላት ኑሮን ያጨለመ፡፡

በጥቂቶች ሴራ ብዙዉን የጎዳ፣
በስቃይ በእንግልት ህዝብን የሚጎዳ፣
የጭቃ ሾህ መስሎ ሰዉን የሚወጋ፣
እርሱ ነዉ ሙስና ሀገር የሚያናጋ፣
ሁላችንም ዛሬ እርሱን እንዋጋ፡፡

ከያብባል አዲስ